ሚያዚያ 29 ቀን 2007 ዓ.ም.

*ጋዜጣዊ መግለጫ*

## አለ በጅምላ በባህር ዳር ከተማ መደብሩን ከፍቶ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡

አለ በጅምላ የእጅ በእጅ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎቱን በመላ አገሪቱ ለማዳረስ በያዘው እቅድ መሰረት ስድስተኛ መደብሩን በከፍተኛ የእድገት ግስጋሴ ላይ በምትገኘው የአማራ ብሄራዊ ክልል ዋና ከተማ በባህር ዳር ከተማ ከፍቶ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡

ድርጅቱ በዛሬው እለት ከፍተኛ የፌዴራልና የክልል የመንግስት የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት በባህርዳር ከተማ መደብሩን ከፍቶ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ የኅብረተሰቡን የፍጆታ ምርቶች ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሲሆን በፍጆታ ምርቶች ላይ የዋጋ ንረት እንዳይከሰትም አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

የመደብሩ አገልግሎት መስጠት መጀመር የቸርቻሪ ነጋዴዎች፣ የሸማቾች ማህበራትና ለተጠቃሚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና ካፌዎች የመሳሰሉ ተቋማትና ሌሎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የሚፈልጓቸውን የተለያዩ የፍጆታ ምርቶች በአንድ ቦታ፣ በአንድ ጣሪያ ስር በአካባቢያቸው ለማግኘት ያስችላቸዋል፡፡

ይህም በእነዚህ ተቋማት የሚገለገሉ የከተማዋና በአካባቢው የሚገኙ ሳተላይት ከተሞች ነዋሪዎች **ጥራት ያላቸው** የፍጆታ ምርቶችን **በተመጣጣኝ ዋጋ** ለማግኘት ያስችላቸዋል፡፡

አለ በጅምላ ለደንበኞቹ የሚያቀርባቸውን የምርት አይነቶችም (SKU) ሲጀምር ከነበሩት 147 በአሁኑ ወቅት ከ 500 በላይ ለማድረስ ችሏል፡፡ ወደፊትም በመደብሮቹ የሚያቀርባቸውን የምርት አይነቶች በማሳደግ ደንበኞቹ፤ ሁሉንም አይነት ምርቶች በአንድ ቦታ፣ በአንድ ጣሪያ ስር ለማግኘት እንዲችሉ ያላሰለሰ ጥረት ያርጋል፡፡

አለ በጅምላ በበጀት ዓመቱ በእቅድ በያዛቸው በአማራ ክልል በደሴ፣ በኦሮሚያ ክልል ጂማና አዳማ፣ በትግራይ ክልል በመቀሌ እና እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር መደብሮቹን በመክፈት በመላው አገሪቱ ተደራሽ ለመሆን የሚያርገውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ይህም በአመቱ መጨረሻ የድርጅቱን መደብሮች ቁጥር አስር ያደርሰዋል፡፡

በቀጣይም በመላ አገሪቱ በርከት ያለ ህዝብ በሚኖርባቸው በተመረጡ 27 ከተሞች ከ36 የሚልቁ መደብሮችን ለመክፈት እቅድ ይዟል፡፡

መሰረታዊ በሆኑ የፍጆታ ምርቶች ላይ የሚከሰተውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋትና ዘላቂ አቅርቦት እንዲኖር ለመስቻል፤ እንዲሁም ዘመናዊ የጅምላና ችርቻሮ የንግድ አሰራር በአገሪቱ ለማስፋፋት እንዲረዳ ታስቦ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት **"አለ በጅምላ"** በሚል የንግድ መጠሪያ የጅምላ ማከፋፈያ መቋቋሙ የሚታወስ ነው፡፡

*ለበለጠ መረጃ ኮርፖሬት ኮሚዩኒኬሽን ዲፓርትመንት*
*አቶ በሪሁን መኮንን፣ ስልክ +251 (0)929 907014/0911 682364፣ ኢ-ሜይል፡ be.mekonnen@alle.et ያነጋግሩ፡፡*